Victorian Equal Opportunity
& Human Rights Commission

# ስለ አድልዎ ፈጠራ መረጃ

## > መብቶችዎን ማወቅና ለቅሬታዎ መፍትሄ ማምጣት

## አድልዎ መፍጠር

የቪክቶሪያ ህግ፣ ሰዎችን ከአድልዎ፣ ከግብረስጋ ድፍረት፣ በደለኛ ከመሆን እና ከዘረኝነትና ሃይማኖታዊ ስም ማጥፋት እንዳይደርስባቸው ይከላከላል።

አድልዎ መፍጠር ማለት የሆነን ሰው አላግባብ ማስተናገድ ይህም እንደሚከተለው ምክንያት ይሆናል:

- በዘር፣ በቀለም፣ በትውልድ ዘር፣ የትውልድ ሃገር፣ የትውልድ ሀረግ ወይም የመጣበት ጎሳ
- በሃይማኖታዊ እምነት ወይም በሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ላይ ተሳትፎ በማድረግ
- አካለጉዳተኛ፣ በሽታ ወይም ጉዳት ማለት ከሥራ ጋር በተዛመደ በደረሰ ጉዳት
- አሳዳጊ በመሆን ወይም ተንከባካቢ በመሆን፣ ለምሳሌ፡ እነሱ ለህጻናት ወይም ለሌላ የቤተሰብ አባላት እንክብካቤ ለመስጠት ሃላፊነት ስላላቸው
- እድሜ፣ ወጣትም ሆኑ በእድሜ ትልቅ ወይም በአጠቃላይ በእድሜ ሳቢያ በማድረግ
- ጾታ
- የሥራና ሠራተኛ እንቅስቃሴ፣ ለምሳሌ፡ ስለ መብቶቻቸው ወይም በሥራ ላይ ያላቸው የሥራ ማእረግ ሳቢያ በማድረግ ጥያቄዎች ወይም አሳሳቢ ነገሮችን ማንሳት
- ኢንዱትሪያል እንቅስቃሴ፣ ማለት የኢንዱስትሪ ድርጅት አባል መሆን እንደ የንግድ ማሕበር ወይም በኢንዱትሪያል እንቅስቃሴ ላይ ተሳታፊ መሆን ወይም በማሕበር ላይ ላለምሳተፍ መወሰን
- የአካል ገጽታ፤ እንደ ቁመት፣ መጠን፣ ጸጉር ወይም በተፈጥሮ ባሉ ምልክቶች ላይ
- ነብሰጡር መሆንና ጡት በማጥባት
- ህጋዊ በሆነ የግብረስጋ እንቅስቃሴ
- ወሲባዊ ገለጻ ወይም በጾታ መለየት፣ በሁለቱም ግብረስጋ ተጠቃሚም ሆነ ወንዳገረድ፣ ሴት ከሴት ጋር ወሲባዊ ግንኙነት የሚያደርግ፣ ሁለት ወሲባዊ ያለው፣ ወሲባዊ የቀየረ፣ ጾታን የቀየረ ወይም የማይታወቅ ጾታ
- የጋብቻ ሁኔታ፣ ቢያገቡም፣ ከዚያ በፊት ቢሆኑም ወይም እንደ ባልና ሚስት ሆኖ አብሮ በመኖር
- የፖለቲካ እምነት ወይም በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ በምንም አካል አለመሆን
- ከነዚህ የግል ባህሪያት ውስጥ በአንደኛው ላይ የተዛመደ ያለበት ወይም ሊኖርበት የሚችል ሰው ይሆናል።

እንዲሁም ወሲባዊ ማስፈራራት ህገ-ወጥነት ነው። በኢሜል ወሲባዊ ሁኔታን መግለጽ ወይም አስተያየት መስጠት፣ ሳይፈልጉ መነካካት ወይም ለወሲብ ጥያቄ ማቅረብ እና ተገቢ ያልሆነ የወሲባዊ ነገር መለጠፍ በዚህ ውስጥ ይካተታል።

## አድልዎ መፍጠር ህገ-ወጥነት የሚያሰኝ የት ላይ ነው

በቪክቶሪያ ውስጥ በሚከተሉት ውስጥ ከተፈጸመ ህገ-ወጥነት ነው:

- መጠለያ
- ክለቦች
- ትምህርት
- ሥራና ሠራተኛ፣ ማለት የትርፍ ሰዓት፣ ሙሉ ቀን፣ የአልፎ አልፎ ሥራ፣ ኮንትራትና ጊዚያዊ ሠራተኞችን እንዲሁም ለሥራ የሚሠለጥኑትን ያካትታል
- እቃዎቻና አገልግሎቶች
- መሬት ሽያጭና ማዛወሪያ
- አካባቢ መንግሥት
- ስፖርት

## የአድልዎ መፍጠር አይነቶች

ቀጥታዊ የሆነ ማዳላት የሚከሰተው አንድ ሰው አላግባብ ሲስተናገድ ምክንያቱም የሰውየው ባህሪ በህግ የተጠበቀ ስለሆነ።

ጆርጅ/George በራሱ ሙያ ሥራ ለማካሄድ የጠበቀውን ለሥራ ቃለመጠይቅ አላገኘም ምክንያቱም በመጣበት የጎሳ/ዘር።

በተዛዋሪ ማዳላት የሚደረገው ሁሉም ሰው በአንድ አይነት መንገድ ሲስተናገድና የሆነ ሰው ይጎዳል ምክንያቱም በግለሰቡ ባህሪ ይሆናል።

የግል ቸኮችን ተቀባይነት ከማግኘታቸው በፊት ደንበኞች በሞላ የመንጃ ፈቃድ በመጋዘን ሃላፊ በኩል ይጠየቃሉ፤ ነገር ግን ራመሽ/Ramesh መንጃ ፈቃድ የለውም ምክንያቱም የማየት ችግር ስላለበት።

## ለአድልዎ ፈጠራ ተብሎ መረጃ መጠየቅ

በአድልዎ ፈጠራ መንገድ ለመጠቀም ተብሎ ስለማንኛውም የተጠበቀ ግላዊ ገጸ ባህሪያት መረጃ መጠየቅ ህገ-ወጥነት ነው።

በሥራ ቃለመጠይቅ ጊዜ አልይ/ Ally ስለማግባቷ ወይም አለማግባቷ ተጠየቀች ከዚያ ልጆች ለመውለድ እቅድ እንዳላት። ምንም እንኳን ለቦታው ጥሩ ሰው ብትሆንም ነገር ግን የሥራ ሥራው ለአልይ/ Ally አልተሰጣትም።

## ስም ማጉደፍ

ስም ማጥፋት/ማጉደፍ ባህሪ ለሌሎች ለመጥላት፣ ላለማክበር ወይም ለአንድ ሰው ወይም ለተሰበሰቡ ሰዎች ለማጎሳቆል ይገፋፋል ምክንያቱም በእነሱ ጎሳ ወይም ሃይማኖት ሳቢያ በማድረግ ነው።

ይህም በንግግር፣ በጽሁፍ፣ በመስመር ላይ ወይም በሆነ ጎሳ ወይም የሃይማኖት ቡድን ላይ የተደባዳቢ ባህሪን ማሳየት ያካተተ ሲሆን ታዲያ ሌላውም እነሱን መሳለቂያ፣ እንዲጠሉ ወይም በነሱ ላይ ሁከትና በንብረታቸው ላይ ጉዳት እንዲደርስና በነሱ ላይ የውሸት ማመልከቻ እንዲደረግ ያባብሳል።

እንዲሁም የሌላን ሰው ስም ለማጉደፍ መፍቀድ ወይም እርዳታ መስጠት ህገ-ወጥነት ሲሆን ለምሳሌ፡ ስለነሱ የጽሁፍ ህትመት በማካሄድ ወይም መረጃ በመበተን ነው።

አንዳንድ ባህሪያት በአግባብና ለጥሩ እምነት ከተደረግ ማለት እንደ ስለ ዘረኝነት በብዙሃን ማሰራጫ ሪፖርት መጻፍ ስም እንደማጥፋት ላይቆጠር ይችላል። ስለ አንድ ሰው ጎሳ ወይም ሃይማኖት አንዳንድ አስተያየቶች ወይም ቀልዶች እንደ ስም ማጥፋት ላይቆጠሩ ይችላሉ፤ ነገር ግን በህጉ ላይ እንደተጠቀሰው በስምንቱ ህዝባዊ ህይወት ውስጥ አንደኛው በሥራ ላይ ከዋለ አድልዎ መፍጠር ሊሆን ይችላል።

## ለአደጋ ማጋለጥ

ይህ የሆነ ሰው ለጎጂ የሆነ ነገር ሲጋለጥ ሲሆን ምክንያቱም ስለነሱ መብቶች በመናገር፣ በነሱ ላይ ቅሬታ በማቅረብ ወይም ሌላ ሰው እንዲከስ በመርዳት ይሆናል። እንዲሁም ለአደጋ ማጋለጥ ህገ-ወጥነት ነው።

## ነቲ ኮሚሽኑ/Commission ቅሬታ/ክሲ ምድላው

በወሲባዊ ጥቃት፣ በአደጋ መጋለጥ ወይም ስም በማጉደፍ አንጻራዊ በሆነ መልኩ አድልዎ ተፈጥሮብናል ብለው ካሰቡ ያነጋግሩን። ስለ ቅሬታ አቀራረብ አሰራር በተመለከተ መረጃ ልንሰድልዎ እንችላለን። ልንረዳዎ ካልቻልን እርስዎን ሊረዳ ወድሚችል በመላክ ልንረዳዎ እንሞክራለን።

እንዲሁም ደብዳቤ ወይም በኢሜል አድርጎ ወይም በእኛ የመስመር ላይ ቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ በማጠናቀቅ ቅሬታ/ክስ ለእኛ ማስገባት ይችላሉ። በራስዎ ቋንቋ አድርገው ቅሬታዎን ማቅረብ ይችላሉ ወይም ሊደውሉልን ይችላሉ ታዲያ ያለዎትን ቅሬታ በመጻፍ ልንረዳዎ እንችላለን። ወደ እኛ ቅሬታ ለማስገባት አያስከፍልም እንዲሁም ይህን ቅሬታ ለማዘጋጀት የህግ ጠበቃ አያስፈልግዎትም።

ላለዎት ቅሬታ መፍትሄ እንዲያገኙ ኮሚሽኑ/ Commission ሊረዳዎ ይሞክራል፤ ነገር ግን ለርስዎም ሆነ ወይም ቅሬታ ላቀረቡበት ግለሰብ ወይም ድርጅት ጠበቃ አንሆንም።

ቅሬታ በሚያስገቡበት ጊዜ፣ ስላለዎት ክስ/ ቅሬታ በማነጋገርና የበለጠ መረጃ እንዲሰጡን ልንጠይቅዎ እንችላለን። ቅሬታዎን በእርቅ ድርድር አማካኝነት መፍትሄ ስለማግኘት መሞከር በማነጋገር እንዴት ለችግሩ መፍትሄ ማምጣት እንደፈለጉ ልናነጋግርዎ እንችላለን።

Victorian Equal Opportunity
& Human Rights Commission

በአጠቃላይ እርስዎ ቅሬታ ላስገቡበት ግለሰብ ወይም ድርጅት Commission ኮሚሽኑ ያነጋግራል፤ ስለዚህ የርስዎን ክስ ወረቀት ቅጅ መስጠትና ያላቸውን አስተያየት መጠየቅ ይሆናል። እነሱም ምን እንዳሉ በክስ ምላሽ ወረቀት ላይ እናሳውቅዎታለን።

በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ለመወሰን የርስዎን ቅሬታ ላናስተናግድ እንችላለን። ይህ ሁኔታ ሲከሰት ታዲያ ለምን እንደሆነ ለመግለጽ እናነጋግርዎታለን።

በአብዛኛው ጉዳዮች ላይ በእርቅ ድርድር በኩል ለቅሬታ መፍትሄ ማስገኛ መንገድ ለርስዎ፣ ቅሬታ ላቀረቡበት ግለሰብ ወይም ድርጅት ለመርዳት እንሞክራለን። እርቅ ድርድሩ በአካል ፊት ለፊት ስብሰባ በማካሄድ፣ በተለፎን ጉባኤ ወይም በኢሜል ወይም በፖስታ መልእክት አማካኝነት አስታራቂ ባሉበት ማካሄድ ይቻላል። ቅሬታዎች በብዙ የተለያዩ መንገዶች መፍትሄ ሊያገኙ ሲችሉ ለምሳሌ፡ ይቅርታ በመጠየቅ፣ ፖሊሲን በመቀየር፣ ሠራተኛን በማሰልጠን ወይም ካሳ በመስጠት ይሆናል።

## ስለ ኮሚሽኑ/ Commission

የ Victorian Equal Opportunity and Human Rights Commission ከማንም ተጽእኖ ነጻ የሆነ ህጋዊ የሆነ አካል ሲሆን በሶስት ህጎች መሰረት ሃላፊነት:

- *Equal Opportunity Act 2010*
- *Racial and Religious Tolerance Act 2001*
- *Charter of Human Rights and Responsibilities Act 2006*

## በ Commission አገልግሎቶች ላይ የሚካተት:

- በነጻ የተለፎን ጥያቄ ማቅረቢያ መስመር
- በነጻና አግባብ ያለው የክርክር አስወጋጅ አገልግሎት
- ስለ እኩልነት መብት እድል፣ የዘረኝነትና የሃይማኖት ስም ማጥፋት እንዲሁም ስለ Charter of Human Rights and Responsibilities መረጃ እና ትምህርት አቅርቦት
- ትምህርት፣ ስልጠና እና የመማክርት አገልግሎቶች።

ስለ እኩልነ መብት እድል እና ሰብአዊ መብቶች መረጃ ለማግኘት እባክዎ ያነጋግሩን።

## ንኣና ንክተዛርብ፡

**ለጥያቄ መስመር**: 1300 292 153
**አስተርጓሚዎች**: 1300 152 494
**ኢሜል**: enquiries@veohrc.vic.gov.au

Level 3, 204 Lygon Street, Carlton Victoria 3053
**ስልክ**: 1300 891 848
**ፋክስ**: 1300 891 858
**መስማት ለተሳነው/TTY**: 1300 289 621
**ብዌብሳይት፡** humanrightscommission.vic.gov.au
**በመስመር ላይ የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ**: humanrightscommission.vic.gov.au/complaints

*የክህደት ቃል: ይህ መረጃ እንደ መመሪያ ብቻ ተብሎ የወጣ ነው። ይህ ህጋዊ ለሆኑ ምክር አይተካም።*

Victorian Equal Opportunity
& Human Rights Commission

**ህትመት** በ Victorian Equal Opportunity and Human Rights Commission, ሰኔ/June 2011ዓ.ም።